**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**

סוג הבחינה: א. בגרות לבתי ספר על־יסודיים
ב. בגרות לנבחנים אקסטרניים
מועד הבחינה: קיץ תשע"ב, 2012
מספר השאלון: 572201, 132

# אמהרית

שתי יחידות לימוד
השלמה מ־3 ל־5 יחידות לימוד

## הוראות לנבחן

א. משך הבחינה: שעתיים.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה: בשאלון זה חמישה פרקים.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | קטע שנלמד | — | 30 נקודות |
| פרק שני | — | לשון | — | 25 נקודות |
| פרק שלישי | — | קטע שלא נלמד | — | 30 נקודות |
| פרק רביעי | — | פתגמים | — | 10 נקודות |
| פרק חמישי | — | הבעה | — | 5 נקודות |
| | | סה"כ | — | 100 נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש: אין.

ד. הוראות מיוחדות: (1) כְּתוֹב את כל התשובות בשאלון עצמו (במקומות המתאימים).
(2) כְּתוֹב את כל התשובות באמהרית ובעט בלבד. אסור למחוק בטיפקס.
(3) בסיום הבחינה החזר את השאלון למשגיח.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

/המשך מעבר לדף/

**שים לב: את התשובות כְּתוֹב בָּרוּר, בעֵט (ולא בעיפרון) ובאותיות גדולות.**

**አስተውል! መልሶችህን በግልፅና በትልልቅ ፊደሎች በእስክርቢቶ ብቻ ጻፍ።**

## פרק ראשון – קטע שנלמד

(30 נקודות)

קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 11-1 שאחריו.

## ክፍል አንድ – የተማሩት ምንባብ

(30 ነጥብ)

ከታች የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ1-11 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልስ።

### ታማኝነት ከሁሉ የበለጠ ነገር ነው

የንጉሥ ግምጃ ቤት (מחסנאי) ሆኖ የሚሠራ አንድ ሰው ነበር፤ እሱም የንጉሡን ንብረት እየሰረቀ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሀብታም ሆነ። ኋላም ብዙ ሀብት መሰብሰቡን የተረዳው ግምጃ ቤት "ከዚህ ሥራ ለቅቄ ነጋዴ ብሆን በጥቂት ጊዜ ውስጥ የባለ ብዙ ሀብት ባለቤት እሆናለሁ" ብሎ አሰበ። ከዚያም ከንጉሡ ዘንድ ቀርቦ "ከእንግዲህ ወዲያ እየነገድሁ መኖር አስቤያለሁና ፈቅደውልኝ ቢያሰናብቱኝ እወድ ነበር" ብሎ ለመናቸው። ንጉሡም "መልሱን በኋላ እሰጥሃለሁ" ብለው አሰናበቱት። ንጉሡ የግምጃ ቤቱ ተቆጣጣሪ ሆኖ የሚሠራውን ሠራተኛ አስጠርተው "ይህ ግምጃ ቤት ሥራውን በትክክል ይሠራል ወይ?" ብለው ጠየቁት። ተቆጣጣሪውም "የጎደለውን ገንዘብ ሁሉ በመዝገብ ይዤዋለሁ የተሰረቀው የገንዘብ ልክ ይህ ነው" ብሎ ለንጉሡ አስረዳቸው።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ግምጃ ቤቱን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ "አንድ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን በጠረጴዛው ላይ አንድ ጠርሙስ ወተት አስቀምጦ ሳይወትፈው ረስቶት ሄደ። ከዚያም አንድ እባብ በጠርሙሱ አፍ ገብቶ ወተቱን በሙሉ ሙጥጥ አድርጎ ጠጣው። ከጠጣውም በኋላ ተመልሶ በጠርሙሱ አፍ ሊወጣ ቢሞክር ሰውነቱ በጣም ደንድኖ ስለነበር የጠርሙሱ አፍ አላስወጣ አለው። እንግዲህ እንዳንተ ሐሳብ ይህ እባብ ከጠርሙሱ ውስጥ መውጣት እንዲችል ምን ማድረግ የሚገባው ይመስልሃል?" ብሎ ጠየቀው።

ግምጃ ቤቱ "የጠጣውን ወተት ሁሉ መመለስ ያስፈልገዋል፤ ይህን ያደረገ እንደሆነ ሰውነቱ እንደቀድሞው ተመልሶ ይቀጥንና የጠርሙሱ አፍ ያስወጣዋል፤ አለበለዚያ መውጣት አይችልም ብሎ መለሰለት። ንጉሡም ግምጃ ቤቱን "ያንተም ነገር እንደዚሁ ያለ ነው" አሉና በምሳሌ አስረዱት። ግምጃ ቤቱ ምሳሌው ስለገባው በስርቆት ላይ የተመሠረተው የባለሀብትነት ምኞቱ ከንቱ እንደሆነ ተረዳ። ለሥራና ለሕይወት ስኬታማነት አንዱ መርህ ሰው በኃላፊነት በተረከበው ሥራው ላይ ታማኝ ሆኖ መገኘቱ ነው።

/המשך בעמוד 3/

**ጥያቄዎች** (30 ነጥብ)

በምንባቡ መሠረት ከ1-11 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ።
(እያንዳንዱ ጥያቄ የያዘው ነጥብ ከጥያቄው መልስ መስጫ ሠረዞች በታች ተጽፏል።)

**השאלות** (30 נקודות)

ענה על השאלות 11-1 באמהרית, לפי הקטע.
(מספר הנקודות לכל שאלה רשום בסופה.)

1. የንጉሡ ግምጃ ቤት እንዴት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሀብታም ሆነ?

______________________________

______________________________

(2 ነጥብ)

2. ብዙ ሀብት መሰብሰቡን የተረዳው ግምጃ ቤት ምን ብሎ አሰበ?

______________________________

______________________________

(3 ነጥብ)

3. ግምጃ ቤቱ ከንጉሡ ዘንድ ቀርቦ ምን ብሎ እንደለመነው ጻፍ።

______________________________

______________________________

(3 ነጥብ)

4. ንጉሡ ግምጃ ቤቱን ምን ብለው አሰናበቱት?

______________________________

______________________________

(2 ነጥብ)

5. ንጉሡ የግምጃ ቤቱን ተቆጣጣሪ ምን ብሎ ጠየቀው?

______________________________

______________________________

(2 ነጥብ)

/המשך בעמוד 4/

6. የግምጃ ቤት ተቆጣጣሪው ለንጉሡ ምን ብሎ አስረዳው?

________________________________________

________________________________________

(4 ነጥብ)

7. እባቡ ለምን በጠርሙሱ አፍ መውጣት አቃተው?

________________________________________

________________________________________

(3 ነጥብ)

8. ግምጃ ቤቱ ስለእባቡ በተጠየቀ ጊዜ ምን ብሎ መለሰ?

________________________________________

________________________________________

(3 ነጥብ)

9. ግምጃ ቤቱ መልስ ከሰጠ በኋላ ንጉሡ ምን አለ?

________________________________________

________________________________________

(2 ነጥብ)

10. ግምጃ ቤቱ በምሳሌ የተነገረው ነገር ሲገባው ምን ተረዳ?

________________________________________

________________________________________

(3 ነጥብ)

11. ለሥራና ለሕይወት ስኬታማነት አንዱ መርህ ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

(3 ነጥብ)

/המשך בעמוד 5/

## ክፍል ሁለት – የሰዋሰው ጥያቄዎች

(25 ነጥብ)

ከ12-21 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልስ።
ለያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት 4 አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ክበብ።
(እያንዳንዱ ጥያቄ 2.5 ነጥብ አለው፣ በአጠቃላይ 25 ነጥብ።)

## פרק שני – לשון

(25 נקודות)

ענה על כל השאלות 12-21.
בכל שאלה הקף במעגל את האות המסמנת את התשובה הנכונה, מבין 4 האפשרויות הנתונות.
(לכל תשובה נכונה — 2.5 נקודות; סה"כ — 25 נקודות)

12. አፄ ቴዎድሮስ የእንግሊዝን ዲፕሎማቶች አሰሩ። ________ እንግሊዞች ተጣሏቸው።
    (ሀ) አለበለዚያ
    (ለ) በመሆኑም
    (ሐ) ነገር ግን
    (መ) ለማንኛውም

13. የሰላም ድርድሩ አልተሳካም፤ ________ ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም።
    (ሀ) ስለነበር
    (ለ) እና
    (ሐ) ቢሆንም ግን
    (መ) ቢሳካም

14. ለመነ ብሎ ልመና ካለ አጨደ ብሎ ________ ይላል።
    (ሀ) አጨዱ
    (ለ) ማጭድ
    (ሐ) ማጨኛ
    (መ) አጨዳ

15. ሄደ ብሎ አካሄድ ካለ ሰጠ ብሎ ________ ይላል።
    (ሀ) ስጦታ
    (ለ) አሰጣጥ
    (ሐ) ሰጪ
    (መ) አቀባበል

16. ተወላገደ ብሎ ወልጋዳ ካለ፤ ________ ብሎ ________ ይላል።
    (ሀ) ተመለጠ ፣ መላጣ
    (ለ) ተመታ ፣ መታ
    (ሐ) ወሬ ፣ ወሬኛ
    (መ) ተቀጠረ ፣ አቃጣሪ

/המשך בעמוד 6/

17. "ምንም ቢሆን የተማረ ወድቆ አይወድቅም" ሲል፤

(ሀ) በማንኛውም ስፍራ ቢሆን የተማረ ሰው ቦታ አያጣም።

(ለ) መንገዱ አስፋልት ባይሆንም የተማረ ሰው ሲሮጥ አይወድቅም።

(ሐ) የተማረ ሰው በትግል ጫወታ የሚችለው የለም።

(መ) መልሱ አልተሰጠም።

18. __________ በማየታችን እጅግ ተደሰትን።

(ሀ) አባታችን

(ለ) እኅታችንን

(ሐ) እኅቶቻችን

(መ) ወንድሞቻችን

19. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ፊደሉ ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ሁለት ትርጉም ያለው ቃል የቱ ነው?

(ሀ) ይጠባል

(ለ) ይላላል

(ሐ) ይሄዳል

(መ) ይገናል

20. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ የመሀከለኛው ፊደል ሲደገም ወደ ብዙነት የሚለወጠው የትኛው ቃል ነው?

(ሀ) ወርቅ

(ለ) ትጥቅ

(ሐ) ትንሽ

(መ) ሽንጥ

21. ኡሪ __________ ዝም አሰኘው።

(ሀ) ዳንኤል

(ለ) ለዳንኤል

(ሐ) የዳንኤል

(መ) ዳንኤልን

/המשך בעמוד 7/

## פרק שלישי – קטע שלא נלמד

(30 נקודות)

קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 22-31 שאחריו רק באמהרית.

## ክፍል ሦስት – ያልተማሩት ምንባብ

(30 ነጥብ)

ከታች የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ22-31 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ።

### ፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ

ፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ በቀንድ-አውጣ (חילזון) አማካኝነት ለሚተላለፈው ብልሃርዚያ ለተባለው በሽታ መድኃኒት ያገኙ የሳይንስ ጠቢብ ናቸው። ፕሮፌሰር አክሊሉ በሐረር ክፍለ ሀገር በጅጅጋ ከተማ እ.አ.አ በ1936 ዓ.ም ተወለዱ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በወቅቱ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እየተባለ ይጠራ ወደነበረው የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በሳይንስ መስክ ትምህርታቸውን አጥንተው በ1955 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አገኙ። ከዚያም የውጪ የትምህርት እድል አግኝተው ወደ አሜሪካን አገር በመሄድ ከጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ በዶክትሬት ዲግሪ ተመረቁ። ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አገራቸው እንደተመለሱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት መሥራት ጀመሩ።

በወቅቱ ወደሰሜን ኢትዮጵያ ለሥራ ጉብኝት ሄደው ሳለ ሰዎች ልብሳቸውን በእንዶድ ሲያጥቡ በእንዶዱ አረፋ ብዙ ቀንድ አውጣዎች ሞተው ተመለከቱ። ቀንድ አውጣዎች የብልሃርዝያ በሽታ ተሸካሚዎች ናቸው። በሽታውም በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፍቶ ስለነበር ሰፊ ጊዜ ወስደው ማጥናት ቀጠሉ። ፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ የምርምር ተባባሪያቸው ከሆኑት ከዶክተር ለገሰ ወልደዮሐንስ ጋር በመሆን ለ25 ዓመታት ካጠኑ በኋላ "እንዶድ 44" በመባል የሚታወቅ መድኃኒት አገኙ። ፕሮፌሰር አክሊሉ ለማና ተባባሪያቸው ዶክተር ለገሰ ወልደዮሐነስ ዓለም አቀፍ እውቅናና ተቀባይነት በማግኘታቸው በ1989 ዓ.ም "ተለዋጭ ኖቤል" የተባለው የስዊድን ሽልማት ተሰጥቷቸዋል። እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችንም በተለያዩ ጊዜያት አግኝተዋል። ፕሮፌሰር አክሊሉ በ1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ከእሳቸው እልፈት በኋላ "አክሊሉ ለማ ፋውንዴሽን" የሚባል ተቋም ተመሥርቶ ወጣት ተመራማሪዎችን በገንዘብ እየደጎመ በማበረታታት ላይ ይገኛል።

/המשך בעמוד 8/

**ጥያቄዎች** (30 ነጥብ)
በምንባቡ መሠረት ከ22-29 ያሉትን
ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ።
(እያንዳንዱ ጥያቄ 2.5 ነጥብ አለው።
በአጠቃላይ 20 ነጥብ።)

**השאלות** (30 נקודות)
ענה על השאלות 29-22 באמהרית,
לפי הקטע.
(לכל תשובה נכונה — 2.5 נקודות;
סה"כ — 20 נקודות)

22. ፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ ምን ለሚባል በሽታ ነው መድሃኒት ያገኙት? በሽታውስ በምን አማካኝነት ይተላለፋል?

______________________________

______________________________

______________________________

23. ፕሮፌሰር አክሊሉ በየትኛዋ ከተማ እና በስንት ዓ.ም ተወለዱ?

______________________________

______________________________

______________________________

24. የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምን ተብሎ ይጠራ ነበር?

______________________________

______________________________

______________________________

25. ፕሮፌሰር አክሊሉ መቼ ነው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙት? የተማሩት የትምህርት መስክስ ምን ነበር?

______________________________

______________________________

______________________________

26. ፕሮፌሰር አክሊሉ በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቁት የት አገርና ከየትኛው ዩኒቨርሲቲ ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

/המשך בעמוד 9/

27. ፕሮፌሰር አክሊሉ ለሥራ ጉብኝት በወጡ ጊዜ ምን ተመለከቱ?

28. ፕሮፌሰር አክሊሉ እና ተባባሪያቸው ዶክተር ለገሰ ምርምሩን ለስንት ዓመታት አደረጉ? ያገኙትስ መድሃኒት ምን በመባል ይታወቃል?

29. ፕሮፌሰር አክሊሉ እና ተባባሪያቸው ዶክተር ለገሰ ምን የተባለ ሽልማት ተሰጣቸው? ሽልማቱስ በምን ምክንያት ተሰጣቸው?

/המשך בעמוד 10/

በትእዛዙ መሠረት 30ኛውን ጥያቄ መልስ።

30. ከታች በምድብ I ከምንባቡ ተወስደው ለተጻፉት 5 ቃላት ተመሳሳያቸውን ከምድብ II ፈልገህ ካገኘህ በኋላ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ላይ ጻፍ።
በምድብ II ውስጥ ሦስት ትርፍ ቃላት እንዳሉ አስተውል።
(ለያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ አንድ ነጥብ፡ በአጠቃላይ 5 ነጥብ።)

ענה על שאלה 30, לפי ההוראות.

30. לפניך שני טורים: טור I וטור II.
בטור I כתובות 5 מילים מהקטע.
בטור II כתובות מילים נרדפות למילים שבטור I.
מימין לכל מילה בטור I כְּתוֹב במקום הריק את המילה הנרדפת לה מטור II.

**שים לב:** בטור II יש 3 מילים מיותרות.
(לכל תשובה נכונה — נקודה אחת; סה"כ — 5 נקודות)

| טור I | | טור II |
|---|---|---|
| ሀ. ጠቢብ | ____________________ | ተረካቢ |
| ለ. እልፈት | ____________________ | ምርምር |
| ሐ. ተባባሪ | ____________________ | አዋቂ |
| መ. መስፋፋት | ____________________ | ዓይነት |
| ሠ. ጥናት | ____________________ | ረዳት |
| | | መብዛት |
| | | ሞት |
| | | መርጋት |

/המשך בעמוד 11/

በትእዛዙ መሠረት 31ኛውን ጥያቄ መልስ።

ענה על שאלה 31, לפי ההוראות.

31. ከሀ-ሠ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበብክ በኋላ በምንባቡ መሠረት እያንዳንዱን **እውነት** ወይም **ውሸት** በማለት ትክክለኛውን መልስ ክበብ።
(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ አንድ ነጥብ አለው፣ በጠቅላላ 5 ነጥብ)

31. בכל אחד מהסעיפים ሀ-ሠ, הקף במעגל את התשובה הנכונה:
**נכון** או **לא נכון**, לפי הקטע.
(לכל תשובה נכונה — נקודה אחת;
סה"כ — 5 נקודות)

ሀ. ፕሮፌሰር አክሊሉ በ1955 ዓ.ም ተወለዱ — እውነት ውሸት

ለ. ፕሮፌሰር አክሊሉ ከውጪ እንደተመለሱ የመምህርነት ሥራ ነው የሠሩት። — እውነት ውሸት

ሐ. ፕሮፌሰር አክሊሉ ለሥራ ጉብኝት የወጡት ወደደቡብ ኢትዮጵያ ነበር። — እውነት ውሸት

መ. ፕሮፌሰር አክሊሉ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዶክትሬት ዲግሪ ተመረቁ። — እውነት ውሸት

ሠ. "አክሊሉ ፋውንዴሽን" ወጣት ተመራማሪዎችን በገንዘብ እየደገመ በማበረታታት ላይ ይገኛል። — እውነት ውሸት

/המשך בעמוד 12/

## **<u>ክፍል አራት – ምሳሌያዊ አነጋገሮች</u>**

(10 ነጥብ)

ከ32-36 ያሉትን <u>አምስት</u> ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟላ። (እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ አንድ ነጥብ አለው። በጠቅላላ 5 ነጥብ)

## **<u>פרק רביעי – פתגמים</u>**

(10 נקודות)

השלם את **<u>חמשת</u>** הפתגמים 32-36.
(לכל השלמה נכונה — נקודה אחת;
סה"כ — 5 נקודות)

32. ሲያጌጡ ______________________።

33. ለተቀማጭ ______________________።

34. ____________________ በርበሬ ተወደስ።

35. መጫር ያበዛች ዶሮ ________________________።

36. ________________________ ምንጭ ያደንቃል።

ከ37-38 ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትርጉም <u>በአማርኛ</u> አብራራ።
(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 2.5 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 5 ነጥብ)

<u>הסבר באמהרית</u> את הפתגמים 37-38.
(לכל הסבר נכון — 2.5 נקודות;
סה"כ — 5 נקודות)

37. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

38. ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ነው ለሃምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

/המשך בעמוד 13/

## ክፍል አምስት ኰ ድርሰት

(5 ነጥብ)

ከ39-43 ካሉት ርዕሶች ውስጥ **አንዱን** መርጠህ ከ10-15 መስመር ድርሰት ጻፍ።
ድርሰቱን በገጽ15-16 ጻፍ።
(ገጽ 14 ን ለድርሰትህ ንድፍ መጠቀም ትችላለህ።)

## פרק חמישי – הבעה

(5 נקודות)

בחר ב**אחד** מן הנושאים 39-43, וכתוב עליו חיבור בהיקף של 10-15 שורות.
כתוב את החיבור בעמודים 15-16.
(לטיוטה תוכל להשתמש בעמוד 14.)

39. የሰላም አስፈላጊነት በእስራኤል።
40. የአየር ብክላን እንዴት መከላከል ይቻላል?
41. ከሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደር ለምን በእስራኤል የተሻለ ትምህርት ያስፈልጋል?
42. የማኅበራዊ ፍትህ (צדק חברתי) አስፈላጊነት።
43. በዘንድሮው ዓመት የሚታየው የአረብ አገሮች ሕዝባዊ ንቅናቄ ምክንያት።

/המשך בעמוד 14/

| በዚህ ገጽ ላይ የድርሰትህን ንድፍ ጻፍ። | לטיוטה השתמש בעמוד זה. |
|---|---|

/המשך בעמוד 15/

| | |
|---|---|
| በዚህ ገጽ 15-16 ላይ ድርሰትህን ጻፍ። | כתוב את החיבור כאן (עמודים 15-16) |

/המשך בעמוד 16/

| | |
|---|---|
| כתוב את החיבור כאן (עמודים 15-16). | በዚህ ገጽ 15-16 ላይ ድርሰትህን ጻፍ። |

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך